https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

??/? /? ? ? 204336
? ? 26/5/2014 ?/?

ዳኞች ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች - ጉምሩክ ኮሚሽን አዳማ ቅ/ጽ/ቤት -ነ/ፈጅ አቶ ጋዲሳ ንጉሱ ቀርቧል

ተጠሪ - ቻይና ኮምዩኒኬሽን ኮንስትራክሽን ካምፓኒ ሊሚትል - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች መጋቢት 9 ቀን 2013 ዓ/ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 200701 የካቲት 12 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ፣ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 259165 ታህሳስ 5 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የኢፌዴሪ ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በመ/ቁጥር B-244 ሰኔ 2 ቀን 2012 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ ተጠሪ የፕሮጀክት እቃ እንዲያስገባ ልዩ መብት አግኝቶ በታማኝነት ለዋጋ አተማመን ትክክለኛ ዋጋ በማቅረብ ቀረጥና ታክስ እንዲከፍል ኃላፊነት የተሰጠው ቢሆንም የተሰጠውን መብት ካለአግባብ በመጠቀም ዋጋ አሳንሶ አቅርቧል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ለተጨማሪ ቀረጥና ታክስ መክፈል ምክንያት በመሆኑ ቀረጥና ታክስ ወለድ ጨምሮ ከፍሎ እያለ በዲክላራሲዮን ውስጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለሰፈሩት ዝርዝር መግለጫዎች ተጠያቂነት ያለበት ሆኖ እያለ ከቅጣት ነፃ ተደረጎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከኢፌዴሪ ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ሲሆን ይግባኝ ባይ የአሁን ተጠሪ ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ይግባኝ ባኝ በዲክላራሲዮን ቁጥር ጠቅሶ የሲቪል ኢንዳስትሪ ፈንጂዎች (አሞኒየም ናይትሬት) ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባሁ ሲሆን የገዛሁት ብቸኛ የፈንጂ አምራች ከሆነው መንግስታዊ ድርጅት ከቻይና ሀገረ ነው፡፡ የሽያጭ ስምምነት የዋጋ ሁኔታ እንዲሁም የፈንጂ ዝርዝር ሁኔታ ለመ/ሰጪ አቅርቤያለሁ፡፡ መ/ሰጪ የዋጋ ዝርዝር አስመጣ ባለኝ ጊዜ በዲ ኤች ኤል በቀጥታ ለሥራ አስኪያጁ እንኪላክ አድርጌያለሁ፡፡ ይሁንና መ/ሰጪ የራሱን ዋጋ ከሰጠ በኋላ የዋጋ ዝርዝር ባዘጋጀሁት ቅፅ መሰረት የተላከ አይደለም በማለት ከጉምሩክ መረጃ ቋት (ኢ. ሲ. ቪ. ኤስ) ውስጥ ዋጋ አግኝቻለሁ ብሎ ዋጋ የሰጠ ቢሆንም ዋጋው 90 ቀን ያለፈው ከመሆኑም በላይ የመረጃ ቋቱ (ኢ. ሲ. ቪ. ኤስ) የዓለምን ዋጋ ያልተከተለ ካለመሆኑም ኢ. ሲ. ቪ. ኤስ ኦቨር ኢንቮይስ አይከለክልም፡፡ መ/ሰጪ ከኢ. ሲ. ቪ. ኤስ አገኘሁ ያለው እቃ ዋጋ ይግባኝ ባይ ካስገባው እቃ የሚመሳሰል ስለመሆኑ ያላረጋገጠና 18% ወለድ መጠየቁም ከህግ ውጪ በመሆኑ ባቀረብኩት ኢንቮይስ መሰረት እንድስተናገድ ሲል ጠይቋል፡፡ መልስ ሰጪ የአሁን አመልካችም ይግባኝ ባይ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባው አሞኒየም ናይትሬት በጉምሩክ መረጃ ቋት ውስጥ ከተገኘው ተመሳሳይ እቃ ጋር ሲወዳደር በመመሪያ ቁጥር 111/08 አንቀጽ 5(2መ) መሰረት 10% በላይ በማነሱ አልተቀበልነውም፡፡ ይግባኝ ባይ እንድያስረዳ ተጠይቆ ያቀረበው የዋጋ ዝርዝር ወደ ሀገር ውስጥ በተለያዩ ዲክላራሲዮን የገቡትን እቃዎች የሚመለከት ነው፡፡ ሆኖም የዋጋ ዝርዝር መላክ ያለበት አጠቃላይ ላኪው ድርጅት የሚያመርታቸውን ምርቶች የሚሸጥበት ዋጋ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የዋጋ ዝርዝሩ ውድቅ ተደርጎ በጉምሩክ መረጃ ቋት መሰረት ተስተናግዷል፡፡ ይግባኝ ባይ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባው ማዳበሪያ አሞኒየም ናይትሬት ሳይሆን ኢንዳስትሪ ፈንጂ አሞኒየም ናይትሬት በመሆኑ የተወዳደረው ከኢዳስትሪ ፈንጂ ጋር ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ መጠየቅ በአግባቡ ነው፡፡ ወለድ የተሰራውም በጉምሩክ አዋጅ መሰረት በመሆኑ የይግባኝ ባይ ቅሬታ ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ የኢፌዴሪ ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን አከራክሮ በመ/ቁጥር B-244 ሰኔ 2 ቀን 2012 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 መሰረት ተደርጎ የወጣው መመሪያ ቁጥር 111/08 አንቀጽ 5(2መ) እንደሚደነግገው በዲክላራሲዮን አቅራቢው የእያንዳንዱ የእቃ ዋጋ እና የጉምሩክ የዋጋ መረጃ ዳታ ቤዝ ውስጥ የሚገኘው አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ እቃዎች አማካይ ዋጋ ሲነፃጸር ያለው ልዩነት በማነስ 10% በላይ ከሆነ በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው ዋጋ ተቀባይነት ላይኖረው ወይም ጥርጣሬ ውስጥ ሊገባ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ መ/ሰጪ ይግባኝ ባይ ያስገባው አሞኒየም ናይትሬት ኢ. ሲ. ቪ. ኤስ ላይ ካለው ዋጋ ሲወዳደር 10 በመቶ በላይ ስላነሰ ውድቅ መደረጉ በህጉ አግባብ ነው፡፡ በኢ. ሲ. ቪ. ኤስ የተወዳደረውም በተገኘው ተመሳሳይ እቃ ዋጋ ሌሎች አስመጪዎች ካስመጡት ተመሳሳይ ዲስክሪፕሽን ያለው እቃ ጋር ሲሆን የተወዳደረውም በ90 ቀናት ውስጥ ከገባው እቃ ጋር ነው የሚል መደሚደሚያ ላይ ደርሰናል፡፡ ወለድ በተመለከተ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 122 በልዩነት የሚፈለግ ቀረጥና ታክስ ላይ ከፍተኛ የንግድ ባንክ የማዳበሪያ ወለድ ተጨምሮ እንደሚሰላ የሚገለጽ ሲሆን የ200 4ኛ ሩብ ዓመት 18% ነው፡፡ ወለዱ በዚሁ መሰረት መሰራቱ ተገቢ ነው፡፡ ቅጣታን በተመለከተ ይግባኝ ባይ ያቀረበው የኢንቮይስ ዋጋ ውድቅ የሆነው ከመ/ሰጪ መረጃ ቋት ጋር ሲወዳደር 10% በላይ ያነሰ በመሆኑ ሲሆን ቀረጥና ታክስ እንዲከፍል የተደረገው በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 122 መሰረት ቅጣት የሚጣለው ለቀረጥና ታክስ ያለመከፈል ምክንያት የሆነው ዲክላራሲዮን አቅራቢው ከሆነ ነው ይላል፡ ይሁንና ይ/ባይ ኢ. ሲ. ቪ. ኤስ ላይ ካለው ዋጋ ጋር ተቀራራቢ ዋጋ አላቀረብክም በሚል በመሆኑ ይ/ባይ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለዋጋው ማነስ ምክንያት ያልሆነ በመሆኑ ቅጣት መጣሉ ተገቢ አይደለም ሲል ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ መ/ሰጪ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ በመ/ቁጥር 259165 ታህሳስ 5 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የሰጠው ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኙን ውድቅ አድርጎታል፡፡ መ/ሰጪ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ በመ/ቁጥር 200701 የካቲት 12 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የሰጠው ውሳኔና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኙን ውድቅ አድርጎታል

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ የአሁን ተጠሪ በታክስና ቀረጥ ጋር በተያያዘ ቅጣት ሊከፍል አይገባም ተብሎ የተወሰነበትን አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 122 አንጻር ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ሐምሌ 16 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአሁን አመልካች ቅሬታ ተጠሪ ከውጪ ያስገባውን እቃ ዋጋ አሳንሶ በማቅረቡ ይሄው ተረጋግጦ ተጨማሪ ታክስና ቀረጥ እንዲሁም ወለድ እንዲከፍል ተደርጓል፡፡ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 122 ለቀረጥና ታክስ ያለመከፈል ምክንያት የሆነው ዲክላራሲዮን አቅራቢው ከሆነ ቅጣት እንደሚጣልበት ይገልጻል፡፡ የአሁን አመልካች ቅሬታ ተጠሪ የግብይት ዋጋ አሳንሶ ማቅረቡ ተረጋግጦ እያለ ቅጣት አይከፍልም መባሉ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 122(2) ለቀረጥና ታክሱ ያለመከፈል ወይም በማነስ መከፈል ምክንያት የሆነው ዲክላራሲዮን አቅራቢው የሆነ እንደሆነ ሳይከፈል በቀረው ቀረጥና ታክስ ላይ 10% ቅጣትና የባንክ ወለድ ተጨምሮ እንደሚከፈል ይደነግጋል፡፡ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 122(2) እንግሊዘኛው ትርጉም “where the payment was deferred due to the fault of the declarant, a penalty of 10% and bank interest thereof shall be paid in addition the duties ande taxes.” በሚል ተቀምጧል፡፡ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 122(2) ለቀረጥና ታክሱ ያለመከፈል ወይም በማነስ መከፈል ምክንያት የሆነው ዲክላራሲዮን አቅራቢው የሆነ እንደሆነ ….የሚለው አባባል ቅጣት ለመጣል ዲክላራሲዮን አቅራቢው ያቀረበው ዋጋ ከመረጃ ቋቱ ውስጥ ከተገኘው እቃ ዋጋ ማነሱ ብቻ በቂ ነው የሚል ሳይሆን ዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው የግብይት ዋጋ ማነስ ምክንያት በዲክላራሲዮን አቅራቢው ጥፋት የተፈጠረ እንደሆነ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ግብር ይግባኝ ኮሚሽን እንደተረጋገጠው የአሁን ተጠሪ የቀረበው የግብይት ዋጋ ከአሁን አመልካች የመረጃ ቋት አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ እቃ ዋጋው ማነሱ እንጂ የአሁን ተጠሪ በፈጠረው ጥፋት ስለመሆኑ አንድም የቀረበ ክርክርም ማስረጃም የለም፡፡ በመሆኑም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ግብር ይግባኝ ኮሚሽን ከዚሁ አንጻር አይቶ የሰጠው ውሳኔና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም የአሁን አመልካችን የይግባኝ ቅሬታ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ትእዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

**ውሳኔ**

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 200701 የካቲት 12 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ፣ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 259165 ታህሳስ 5 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የኢፌዴሪ ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በመ/ቁጥር B-244 ሰኔ 2 ቀን 2012 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

ማ/አ　　　　　　　　　　የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም